# የእናት ባንክ የወደፊት ዋና መሥሪያ ቤት ሕንፃ አርክቴክቸራል ዲዛይን አሸናፊ ተመረጠ!

መጋቢት 4 ቀን 2013 ዓ.ም በሸራተን አዲስ ሆቴል በተዘጋጀ ፕሮግራም የእናት ባንክ አ.ማ የወደፊት የዋና መሥሪያ ቤት የሕንፃ ግንባታ አርክቴክቸራል ዲዛይን አሸናፊ ተመረጠ። ተወዳዳሪ ከነበሩት 13 አርክቴክቸራል ዲዛይኖች ባንኩ ለህንፃ ግንባታ ሦስት ዲዛይኖችን በመምረጥ ከአንድ እስከ ሦስት ለወጡ አሸናፊዎች ሽልማት ሰጥቷል። አንደኛ የወጣው አርክቴክቸራል ዲዛይን 35 ወለል እና 140 ሜትር ርዝመት ያለው ዲዛይን ነው። በፕሮግራሙ ላይ የመጀመሪያዋ የባንኩ የቦርድ ሰብሳቢ የሆኑትና በአሁኑ ሰዓት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚደንት ወ/ሮ መአዛ አሸናፊ፣ የባንኩ መስራቾች፤ የባንኩ ቦርድ ሰብሳቢ ወ/ሮ ሀና ጥላሁን እና ሌሎች የቦርድ አባላት እንዲሁም የባንኩ ፕሬዚደንት አቶ ኤርሚያስ አንድአርጌ፣የሥራ አመራር አባላትና ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች በተገኙበት የአርኪቴክቸራል ዲዛይን ውድድር የሽልማት ሥነ ሥርዓት ተከናውኗል።

